የምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዝያ/2015

አዲስ አበባ

ማውጫ

ቁጥር	ርእስ/ንኡስ ርእስ	ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	3
1.1.	የጥቱ ዳራ (Backgraound of The Study)	3
1.2.	የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ	4
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	5
1.4.	የጥናቱ ወሰን	5
1.5.	የጥናቱ አስፈላጊነት	6
1.6.	መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች	6
ክፍል ሁለት	የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ	7
ክፍል ሶስት	የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ	8
3.1.	የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research Design)	8
3.2.	የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)	8
3.3.	መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data Collection Methods)	8
3.4.	የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ	10
ክፍል አራት	የሙስና ስጋት መረጃዎች ትንተና	11
4.1.	የተቋማት አደረጃጀት	11
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	15
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	18
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	19
4.5.	የተቋማት ንብረት አስተዳደር	21
4.6.	የግዥ አስተዳደር	22
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	24
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	26
4.9.	ኦዲትና ቁጥጥር	27
4.10.	የሙስና ስጋት ልየታ	29
ክፍል አምስት	መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	32
5.1.	መደምደሚያ	32
5.2.	የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	33

ክፍል አንድ

መግቢያ

1.1 መግቢያ

የህዝብ ምክርቤቶች (Parliaments) ዋናው የመንግስት ክፍለ በመሆን ህጎች እና ፖሊሲዎች በማውጣት ተግባራዊነታቸው የማረጋጥ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ የህግ አውጪነት ሚናቸው በአንድ አገር ውስጥ የተረጋጋ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲኖር ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የተለያዩ ተቋማት በስራቸው በማቋቋም ህግ የማውጣት እና ተፈፃሚነቱን የመከታተል ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት በተለይ አስፈፃሚን የመንግስት አካል የመቆጣጠር ሚናቸው መጫወት ካልቻሉ አሰፈፃሚው አካል ስልጣኑን አለግባብ ጥቅም ላይ ሊያወለው ይችላል፡፡ ይሁንእንጂ ይህን ሚናቸውን መጣት ካልቻሉ የመንግስት መዋቅር ለሙሰናና ብልሹ አሰራር የተጋለጠ እንዲሆን ሊያደርገው እንደሚችል እሙን ነው፡፡ አስፈፃሚው አካል የሚያስተዳደረው የህዝብ ገንዘብና ንብረት መጠን አንፃር ስንመለከተው ሊያደርሰው የሚችለው አደጋ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡

የፌዴራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ካለፉት ሁለት አመታት ጀምሮ በፌዴራል የመንግስት ተቋማት ደረጃ ሙስና እና ብልሹ አሰራራሮችን የመከላከል አዲስ አቅጣጫ እና ስትራተጂ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ ከተሰጠው ሃለፊነትና ተግባር ውስጥ በመንግሰት ተቋማት ላይ የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት ሁኔታ ዳሰሳዊ የጥናት ማካሄድ ነው፡፡ ይህን ለመወጣት የውስጥ አቅም በመጠቀም እና ከአጠኚ ተቋማት ጋር በመተባበር እያካሄደ ይገኛል፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነት የመንግሰት ተቋማት እንደየ ስራ ባህሪቸው፣ ስልጣንና ኃላፊነት ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ተቋማትን በዘርፍ በማደራጀት የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋቶች የመለየት ስራ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡

በዚህ አዲስ አቅጣጫ መሰረት በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ ለሁለተኛ ጊዜ ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት በማካሄድ ላይ ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ሪፖርት የሚሸፍነው የምክር ቤት ዘርፍ የተካተቱት ስምንት የመንግስት ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህም የህ/ተ/ምክር ቤት፣ የፌደሬሽን ም/ቤት፣ የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የፌደራል ዋና ኦዲት፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት በአንድ ዘርፍ በማካተት የተቋማት የመሙስና ስጋት ጥናት ተካሂዷል፡፡ እንደሚታወቀው እነዚህ ተቋማት የሀገሪቱን ህግ በማውጣት፣ የወጡ ህጎች እንዲተገበሩ የማድረግ፣ የዜጎች መብትና ጥቅም እንዲሁም ሃሳብን በመግለፅ ነፃነትን የሚያስከብሩ ተቋማት በመሆናቸው ከሌሎች የመንግስት ተቋማት በበለጠ ከሙስናና ብልሹ ተግባራት የፀዱ እንደሆኑ የቅርብ ምልከታና ክትትል ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ ይህም የጥናት ሪፖርት በተለዩ አስራ አንድ መሰረታዊ ጉዳዮች በዘርፉ ላይ የሚታዩ የሙስናን ስጋት ሁኔታዎች የቀረቡበት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መሰረታዊ ሃሳብ/ ኣላማ እንዲሁም ኮሚሽኑ እየተከተለ ካለው የጥናት አቅጣጫ በመነሳት በምክር ቤት ዘርፍ የተመደቡት ተቋማትን እንደ አንድ የጥናት ፓኬጅ በመውሰድ ይህ የጥናት ሪፖርት ተጠናቅሯል፡፡ የዘርፉ ተቋማትን የሙስና ስጋት ሁኔታ ማወቅ፣ ችግሮችን መለየት እና በመጨረሻም ለተለዩ ችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ የተቻለው የእያንዳንዱን ተቋም የስራ ሂደቶች፣ አሰራር እና ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በመዳሰስ ነው፡፡ በዚህ መረጃ በማሰባሰቢያ ሂደት የሙስና መከላከል የሚያስችሉ የስነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃት፣ ጠመፈፀም ቁመና፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመደገፍና በማገዝ ሚና ያላቸውን የኮሚቴ አደረጀጀቶች እና ሌሎች የስራ ክፍል ክፍሎች እና አወቃቀር ለመዳሰስ የቻለ ጥናት ነው፡፡ የተዘጋጁ የመረጃ መሰብሰባያ ስልቶች በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በግላቸው ለየት ባለ መልኩ ለሙስናና ብልሹ ተግባራት ሊያጋልጡ የሚችሉ ሊያጋልጡ የሚችሉ ጉዳችዮችን ለቅሞ እንዲትም በአጠቃላይ እንደ አንድ ዘርፍ ተመሳሳይ የሙስና ስጋት ክፍተቶች በመለየት ለተለዩ ችግሮች ምክረ ሃሳቦችን በሚጠቁም መልኩ የቀረበ ጥናት ሪፖርት ነው፡፡

ሙስና በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ወይም ተቋማትን የማፍረስ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን የተለዋዋጭነት ባህሪ እያሳየ ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

1.2 የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

በዚህ ጥናት የምክር ቤት ዘርፍ በሚል የተካተቱ ተቋማት ስምንት ሲሆኑ እነዚህም ሶስቱ ተቋማት በሃገሪቱ ህግ በማውጣትና ህገ መንግሰት በመተርጎም ከፍተኛ ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸውን፣ ሁለቱ የዜጎችን መብትና ጥቅም ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ፣ ሁለቱ የሚዲያ አካላት እና አንድ የቁጥርና ክትትል ኃላፊነት ያከለው ተቋማትን ያካተተ ዘርፍ ነው፡፡ እነዚህም ተቋማት የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤ፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠበቂ ተቋም፣ የፌዴራል ዋና አዲት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን) የጥናት መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡ የምክር ቤት ዘርፍ በራሳቸው በውስጥ አሰራራቸው ሙስናና ብልሱ ተግባራትን በመከላል በማስተካከልና በመከላከል ምሳሌያዊ ስራዎችን ከመስራት በላይ ካለባቸው ሃገራዊ ተልዕኮ አኳያም የሃገርን ልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት በማደናቀፍ ከፍተኛ ችግር የሆነውን የሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመዋጋት የጎላና የላቀ ሚና ሊወጡ የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

1.3 ጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ግምገማዊ ጥናት ዋና ዓላማ በምክር ቤት ዘርፍ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡-

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት፤ የፌደረሽን ምክርቤት የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤ፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠበቂ ተቋም፣ የፌዴራል ዋና አዲት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣንላይ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡ ምን እንኳን የምርጫ ቦርድ በዚሁ ዘርፍ ውስጥ ቢካተትም በተለያዩ ምክንያቶች ሚያስፈልጉ መረጃዎች ባለመገኘታቸው ከዚህ ጥናት ውጪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ ነው፡፡ ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፡፡

በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው፡፡ ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በምክር ቤት ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማት የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.6 መረጃው በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናት ሥራው የተካሄደው ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሠራር ከመከላከል ረገድ ሊያከናዉኗቸው የሚገቡ ተብለው በተለዩ የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሲሆን በተጠየቁት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን የተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመጠየቅ መረጃ ሲበሰብ አንዳንድ ተቋማት ውስጥ የሚፈለጉና መረጃ የሚሰጡ የሥራ ኃላፊነት በቀጠሮ ምልልስ ማጋጠሙ፣ በተቋማት መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅቶ ባለመያዝ በተናጠል ለመሰበሰብ መቸገር፣ ሥራውን የሙስና ወንጀል ምርመራ አድርጎ በመውሰድ መረጃ ለመስጠት የማንገራገር ሁኔታዎች በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ተግደራቶች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

የሙስና ስጋት ጥናት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

በዘመናዊ ዴሞክራሲ የሕግ አውጭ አካላት አባላት የሚሾሙት በሕዝባዊ ምርጫ ነው፡፡ ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ ህግ አውጭው የመራጮችን ፍላጎት ብቻ ማገልገል ያለበት ቢሆንም የተደራጁ የፍላጎት ቡድኖች ብዙውን ጊዜ ለፖሊሲ ጥቅማጥቅሞች ሲሉ ገንዘብ ወይም መረጃ በሚሰጡ ህግ አውጪዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ይሞክራሉ በርካታ አጥኚዎች እንደሚግልፁት የፖለቲከኞችን ባህሪ በመቅረጽ እና ህግ አውጪዎች ስልጣናቸውን አላግባብ እንዳይጠቀሙ ተቋማዊ አደረጃጀቶች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ምክርቤቶች ህግ ማውጣትና ተግባራዊነቱን የመከታተል ሃላፊነት ለመወጣትም የተለያ አደረጃጀቶች ያቋቁማሉ (Cecilia, 2003)፡፡ ሆኖም ፖለቲካ ድርጅቶች ስልጣን ለመያዝ በምርጫ መሳተፋቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ከምርጫ አፈፃፀምና ገንዘብ ምንጭ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ስጋቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የመንግስት ሰራተኞች ለገዥ ፓርቲ እንዲመርጡ ማስገደድ በተወሰነ መልኩ የመከሰት እድል አለው፡፡በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ የመንግስትን ግነዘብና ሃበት ለምርጫ ቅስቀሳና ማስፈፀሚያ የመጠቀም ዝንባሌም አንዱ ስልጣን አላግባብ መጠቀም ያስከትላል (Harutyunyan, 2021)፡፡

ፖለቲከኞችና የህዝብ ተወካዮች ለሙስና የመጋለጥ እድላቸው በተለይ በአላደጉ አገሮች የሰፋ ነው፡፡ በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የፓርላማ አባላት የሚከፈላቸው ዝቅተኛ ክፍያ ከሁሉም በላይ የሙስና ምንጭ እንደሆነ ተለይቷል፡፡ ምርጫዎች ውስጥ መሳተፍ ውድ በመሆኑም ተመረጮች ለምርጫ ዘመቻዎች ግብዓቶችን በማሰባሰብ ሂደት አላስፈላጊ አንዳንዴም ከህግ በተፃረረ መልኩ እንቅስቃሴ ሊደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ በተጨማሪም መራጮች ተወካዮቻቸው ላይ ተፅኖ በማሳደር ለሙስና ተጋላጭ ሊያደርጋቸው መቻሉ ታሳቢ ማድረግ ይጠበቃል (Davies, 2009)፡፡ አንዱና ዋነኛው የህዝብ ተወካዮች የሚሰሩ ጉዳይ ቢኖር የህዝብ ፖሊሲዎች ማውጣት ዜጎች ከመንግስት ተግቢውን አገልግሎት ማገዝ ይጠበቅበታል፡፡ በአብዛኛውም የዜጎችን የዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጥራት ይወስናሉ፡፡ሆኖም ከዚህ በተፀራሪ ተወካዮች የተሰጣቸውን ሃላፊነት ባለመወጣት ለግልና ቡዱናዊ ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ የህግ አወጣጥ ስርኣቱን ሊያውሉት ይችላሉ፡፡ የሚወጡ ህጉች የህዝቡን ጥቅም ወደ ጎን በመተው በመንግስትና ዜጎች ያለውን ትምምን ይቀንሰዋል፡፡ ይህም የህግ አወጣጡ ስርኣት ለፖሊሲ ካፕችር (Policy Capture) ተጋላጭ ያደርገዋል (OECD, 2017) ፡፡

ክፍል ሶስት

የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

3.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በዋነኝነት በሁለቱም ህገመንግስታዊ ምክርቤቶችና በስራቸው ባሉ ተጠሪ ተቋማት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

3.3.1. የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

3.3.2. የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሽበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመገምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

3.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኋላ የማደራጃት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውታት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣ ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙሰና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል አራት

የሙስና ስጋት መረጃዎች ትንተና

የምክር ቤት ዘርፍ የስራ አፈጻጸምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት አደረጃጀት ስር የተለያዩ ተመጋጋቢ ጉዳዮች የተዳሰሱ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት ገፅታ በሚመለከት የቀረበው ቀዳሚ ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዘርፉ ካሉ ተቋማት መካከል በስድስት ተቋማት በቋሚነት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 ህግ መሰረት መደራጀታቸውን መመልከት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በተለያዩ ምክንያቶች ከስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊነት በለቀቁ ሁለት ተቋማት በውክልና የተያዙ መሆኑን ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ያም ሆኖ በዘርፉ ካሉ ስምንቱ ተቋማት መካከል በአንዱ ተቋም ብቻ የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ በሰው የተደራጁ ሲሆን (በህጉ መሰረት በሶስት ባለሙያዎች እና በስራ መሪ/ዳይሬክተር በድምሩ በአራት የሰው ኃይል) ፣ በተቀሩት ሰባቱ ተቋማት በአንድ የስራ ኃላፊ የሚመሩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ በዚሁ ተቋማዊ አደረጃጀት የተዳሰሰው ሌላው ጉዳይ የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ራሳን ችሎ የተመደበ ዓመታዊ በጀት መኖሩን የሚመለከት ሲሆን በሁሉም የተቋሙ ሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ለክፍሉ የተመደበ ራሱን የቻለ በጀት አለመኖሩን መገንዘብ ቢቻልም በተፈጠረው አዲስ የበጀት አጠቃቀም ስርዓት መሰረት ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በማቀናጀት በሚመደብ ‹የፑል› አሰራር ስርዓት ወይም ሲስተም የሚጠቀሙ መሆኑን ከተደረጉ ውይይቶችና ከተቋማት ዓመታዊ እቅድ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በዚህ የገንዘብ አጠቃቀም ስርዓት መሰረት አንዳድ ስራዎችን ለመስራት ለምሳሌ ስልጠና ለማካሄድ ከተፈለገ ‹‹ፕሮፖዛል›› ለተቋሙ ስራ ኃላፊ በማቅረብ የማስፈቀድ አሰራር መኖሩን ቢገልፁም ከሌሎቹ ተቋማት የተሻለ አደረጃጀት ያላቸው ተቋምትም ቢሆኑ ላለፉት ሁለት አመታት፣ ዓመታዊ የፀረ-ሙስና ቀንን ከማክበር ውጪ የተዘረጋውን የፖል የገንዘብ አጠቃቀም ስርዓት በመጠቀም የሰሯቸው ስራዎች አጥጋቢ እንዳልሆነ ከተገኙት መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በቢሮ አደረጃጀት እና ቁሳቁስ ማሟላት በኩል ለስራ የሚሆኑ መሰረታዊ እና አስፈላጊ ቁሳቁሶች ወይም የስራ ግብዓቶች የተሟሉላቸው መሆኑን መመልከት ቢቻልም፣ በተለያዩ የቢሮ እጥረት፣ የተቋማት ህንፃ መቀያየር ወዘተ..ምክንያቶች አብዛኛዎቹ የስራ ክፍሎች የያዙት ወይም የሚሰሩባቸው ቢሮዎች ክፍሉ የተሰጠውንና የሚጠበቅበትን ተልእኮ እና የእለት ከዕለት ተግባራት ለማከናወን (ጥቆማ ለመቀበል፣ መረጃ ለመያዝና ለማደራጀት) አዳጋችና አስቸጋሪ እያደረገው መሆኑን መመልከት ተችለሏል፡፡

ዓመታዊ እቅድን በማዘጋጀት ረገድ የዘርፉ ተቋማት አብዛኛዎቹ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ዓመታዊ እቅድ እንደሚያዘጋጁ ወይም እንዳለቸው በመረጃ ማረጋገጥ ቢቻልም፣ከላይ በተቀመጠው በአደረጃጀት ችግር ምክንያት የተወሰኑት ሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ዓመታዊ የስራ ዕቅድ እንደ ሌላቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ዓመታዊ እቅድ ያላቸውም ቢሆኑም ባዘጋጁትና ባፃደቁት ዕቅድ መሰረት ስራዎችን ስለማከናወናቸው የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም የስራ ክፍሎችን ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ውጤታማ ሊያደርቸው የሚችለው አንዱ ስልት አስፈላጊ ከሆኑ ከተቋማት አንዳንድ ክፍሎች ለአብነት ያህል ከህግ ክፍል፣ ከኦዲት፣ ሰው ሃብት ወዘተ… ጋር በቅንጅት መስራት ሲሆን በዚህ ረገድ የክፍሉ ባለሙዎችና የስራ ኃላፊዎች በግል ፈቃደኝነት እና ግንኙነት ላይ የተመሰረተ የመደጋገፍና የመረዳዳት አሰራር ካልሆነ በስተቀር በመመሪያ ወይም በውስጥ አሰራር ህግና ስርዓትን መሰረት ያደረግ በተዘረጋ መደበኛ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ሁሉም በሚባል ደረጃ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከሚረዱ ውስጣዊ አደረጃጀቶች ማለትም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፒሊን ኮሚቴ፣ የግዢ ኮሚቴ፣ የስርዓተ ጾታ፣ የህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ወዘተ መደራጀታቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተቋማት በሚከናወኑ ማንኛውም ውሎች ከመፈረማቸው በፊትና ከተፈረሙው በኋላ በህግ ክፍሎች ሙያዊ አስተያየት እንደሚሰጥባቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለጣልቃ ገብነት በተነሳው ሃሳብ የተሰጡ ምላሾች የዘርፉ ተቋማት በሚከናውኗቸው ማንኛወም ዓይነት ስራዎች የማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት እንደሌለ የተገለፀ ሲሆን ይህ ማለት ግን በይበልጥ የስነ ምግባ መከታተያ ክፍሎች በአግባቡ ቢደራጁ እንዲሁም በሚጠበቁት ልክ ኃላፊነታቸውን ቢወጡ ኖሮ ከጣልቃ ገብነት ነፃ ናቸው የሚል ሃሳብ ሊቀርብ ይችል ነበር ወይ የሚለው ለጥያቄ የሚቀርብ እና ለተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሌለው በተቋማዊ አደረጃጀት የተዳሰሰው ጉዳይ ሙስናና ብልሹ አሰራን በመከላከል እና ስነምግባር መከታተያ ክፍሉን ውጤታማት በማሳደግ የላቀ ፋይዳ ስላለው የጥቆማዎች መቀበያ ስርዓትን ሁኔታን የሚዳስሰው ነው፡፡ በዚህ ረገድ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን የሚመለከቱ ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ጥቆማዎችን (የጥቆማ መቀበያ ሳጥን፣ድረ ገፅ፣የህትመት ውጤቶች) የማሳወቅ ስርዓት መዘርጋታቸውን መመልከት ተችሏል፡፡ ሆኖም በነዚህ መንገዶች የቀረቡ ጥቆማዎች መጠን፣ ዓይነትና ለቀረቡ ጥቆማዎች ስለተሰጡ ምላሾ በተደራጀ መንገድ የተያዙ መረጃዎች አልተገኙም፡፡

በአጠቃላይ በተቋማዊ አደረጃጀት ስር ለሰፈሩ ሃሳቦች መረጃዎች የሚሳዩት/ የሚያስረዱት በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ከማጠናከር ጀምሮ በአጠቃላይ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ለሚስተዋሉ በርካታ ክፍተቶች ዓይነተኛ ምክንያቶች መካከል የተቋማት የስራ ኃላፊዎች ለስነምግባር መከታተያ ክፍሉን የሚሰጡት ትኩረት ድጋፍና ክትትል አነስተኛ መሆን፣ የስራ ክፍሉ የስራ ኃላፊ ተጠሪነትንና አመዳደብ ወይም አደረጀጃት መቀያየር፣ ምቹ የስራ ቢሮዎች አለመኖር፣ የስራ ክፍሉ ኃላፊዎች አቅም እና የባለሙያዎች ብቃትና እጥርት በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ ተቋማት ከተገኙ መረጃዎችና ከትንተናው መገንዘብ የሚቻለው የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች በሚፈለገው አደረጃጀት በጥሩ ቁመናና ሁኔታዎች ውስጥ እንዳልሆኑ ነው፡፡ በአብዛኛው ተቋመት ውስጥ በቂ በጀትና የሰው ሃይል ኖሯቸው የተደራጁ የስምግባር ክፍሎች እንደሌሉ ይታያል፡፡ ይህ ማለት የስነምግባር ክፍሎቹ ሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል ረገድ ከፍኛ ውስንነት የሚስተዋልባቸው እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲሁም ስነ ምግባርን በማስረፅ ረገድ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ አለመሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ ጉዳዩ አሳሳቢ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሕግ አውጪው አካል የሚያወጣቸውን ህጎች ተግባራዊ በማድረግ ለሌሎች ተቋማት ምሳሌ መሆን ሲገባው ይህ ሃላፊነት ባለመወጣቱ ትዝብት ላይ ይጥለዋል፡፡ ውስጣዊ ተቋማዊ ጥንካሬ መፍጠር ያልቻል ህግ አውጪ አካል የተወሳሰበውን የአስፈፃሚው አከል ስራ ለመከታተልና መቆጣጠር የሚያስችል አቅም ሊኖረው አይችልም፡፡ በተለይ የስነምግባር ክፍሎች ስራዎቻቸውን በእቅድ ለመምራት የበጀት አጠቃቀም ስርአቱ እክል ሊፈጥርባቸው ይችላል፡፡ ተጠሪነታቸው ቀጥታ ለተቋሙ አመራር ስለሆነም ለሚሰሩት ስራ በጀት ለማስፈቀድ በሚቀሳቀሱበት ጊዜ ለአመራሩ ጣልቃ ገብነት የተጋለጡ የመሆን እድላቸው የሰፋ ነው፡፡ የሚከውኑት ስራዎች በአመራሩ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ስለሚያደርገው አመራሩ ጥቅሙን አደጋ ላይ የሚጠጥሉ መስሎ ሲሰማው የመከላከል ስራዎች ተገባራዊ እንዳይሆኑ በጀት በመከልከል ለጥቅም ግጭት ተጋለጭ ያደርገዋል፡፡
- በተቋማት የተጠያቂነት አሰራር ከሚያሰፍኑት ስርዓቶች መዋቅሮች መካከል የተለያዩ የስራክፈሎች እና ኮሚቴዎች ማደራጀት አንዱ ነው፡፡ መደራጀታቸው ብቻ በቂ ስለማይሆን ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ውጤቱታማ የሚከላከል ስራ እዲከውኑ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ከተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚታየው እነዚህ የስራ ክፈሎችና ኮሚቴዎች መደበኛ አሰራር ተዘርግቶ ቅንጅታዊ ሙስናንና ብልሹ አሰራሮች የመከላከል ስራ እየተሰራ አለመሆኑን ነው፡፡ ይህ ከአመራሩ ክትትልና ድጋፍ ማነስ ሊኖን ይችላል፡፡

የተደራጁትም ቢሆኑ በተናጠል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ ውጤታ ስራ ስለመከወናቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በቀጣይም ሚናቸውና ውጤታቸው ሊዳሰስ ይገባዋል፡፡

- የስነምግባር ክፍሎች በበላይ ሃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት የተገመገመ አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በኩል ውስንነት መኖሩን መመልከት ይቻላል፡፡ በዕቅድ የሚመራ ሙስናን የመዋጋት ስራ እዳይኖር በማድረግ እክል ሊፈጥር መቻሉ የሚጠበቅ ነው፡፡ የተቋም አመራር አሳታፊ በሆነ መልኩ ሙስናን ለመዋጋት ያለው ዝግጅነት አነስተኛ መሆኑን አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

በዘርፉ የሚገኙ የተቋማት ስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ቀዳሚ ኃላፊነት ከሆኑት መካከል አንዱና ቀዳሚው በተለዩ ርዕሶች፣ ጉዳዮችና የስራ ሂደቶች ዙሪያ የሙስና ስጋት ወይም የአሰራር ስርዓት ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በነዚህ ጥናቶች የተለዩ ክፍተቶች ላይ ተመስርተው የሚሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋማት ከሙስናና ብልሹ ተግባራት የመከላከል አቅማቸውን ማሳደግ እና ተቋማዊ ገፅታቸውን መልካም ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ ሃሳብ ጋር በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት መካከል በአራት ተቋማት በተለያዩ ጉዳዮች/ ርዕሶች የሙስና ስጋት ወይም የአሰራር ስርዓት ጥናቶች ከማካሄድ ውጪ በሌሎቹ የዘርፉ ተቋማት ጥናቶች አለመካሄዳቸውን ነው፡፡ ጥናት ያካሄዱ ተቋማት አንድ በጎ እርምጃና እንቅስቃሴ ሆኖ ቢስተዋልም በጥናቶቹ ለተለዩ ክፍተቶች እና ክፍተቶቹ የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ስለተግባራዊነታቸው ወይም ውጤታቸው የተደራጀ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በዘርፉ በሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ቀድሞ የመከላከል ስርዓት ያልተጠናከረ መሆኑ፣ ስለ ሚሰጡት አገልግሎት ደረጃ እና ገፅታ በገለልተኛ አካል ያስጠኑ ስለመሆኑ ማስረጃ አልተገኘም፡፡

ነገር ግን ተቋሞቹ ስለሚሰጧቸው አገልግሎት፣ በስልጠናዎች፣ በውይይት መድረኮች እና በመገናኛ ብዙሃን አስተያየቶች ለማወቅ ከሚደረግ ጥረት ውጪ መደበኛ የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት እንዳላካሄዱ ማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የተዘጋጁበት እና የታተሙበት ጊዜ የቆየ ቢሆንም (ከ5 ዓመት በፊት) የሰራተኞች ስነ ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ ማዘጋጀታቸውን ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ የስነ ምግባር ደንብና በደንቡ የተካተተቱትን እሴቶች መሰረት በማድረግ ስለተሰጡ የአቅም ግንባታ ወይም የግንዛቤ ስራዎች የተደራጀ መረጃ አልተገኘም፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት በ22 የተለያዩ የስነ ምግባር ነክ ጉዳዮች ላይ ክሰ የቀረበ ሲሆን ነገር ግን ከባድ የዲሲፒሊን ጉድለት ክስ የሚመለከቱ ጉዳዮች የሌሉ መሆናቸውን መመልከት እና ከተደረጉ ውይይቶች መረዳት ተችሏል፡፡ ከነዚህ የክስ ቅሬታ ሃሳቦች ጋር ተያይዞ በየተቋማቱ በቅጥር፣ በእድገት፣በምደባ ወዘተ..የቀረቡ ቅሬታዎች ስለመቅረባቸው መረጃ አልተገኘም፡፡ በነዚህ መሰረታዊ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ተጨባጭ መረጃ ባይገኝም በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የመልካም አስተዳደር ወይም ብልሹ አሰራር የፀዱ ናቸው ለማለት በማረጋገጫነት ሊቀርብ የሚችል ሃሳብ አይሆንም፡፡ በሌላ መልኩ የተቋማት የስራ ኃላፊዎች የተቋማቸውን የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን የስራ ክንውን ይከታተሉ በሚል ለተነሳው ሃሳብ አብዛኛዎቹ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች እና የተቋማት ኃላፊዎች በሰጡት ሃሳብ የክፍሉን እንቅስቃሴ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንደሚከታተሉ ገልፀዋል፡፡ ለአብነት ያህል በማኔጅመንት ስብሰባዎች፣ በስራ ክንውን ግምገማዎች እና ጊዜውን ጠብቀው በሚካሄዱ የስራ አፈፃፀም ግምገማ መድረኮች የክፍሉን እንቅስቃሴና ተግባራትን ማወቅ የሚችሉበት ሁኔታዎች መኖራቸውን ቢገልፁም ክፍሉ የተሰጠውን ተልዕኮ በመወጣት ረገድ ሰፊ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- *የሙስና ስጋት ትናትና ጥናት በሚመለከት ውስን የዘርፉ ተቋማት በከፊል በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ማከናወናቸው ለማየት የተቻለበት ሁኔታ አለ፡፡ በጥናት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚሳዩ ሰነዳዊ መረጃዎች አለመገኘቱ ስራው ተገቢው ትኩረት የተሰጠው አለመሆኑን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ብልሹ አሰራሮችና ሙስናን ለመዋጋት የሚያግዝ የተገልጋዮች እርካታ ላይ ተመስርቶ በገለልተኛ አካል የተደረገ ጥናት አለመኖሩ የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህ ተጠያቂነት ለማስፈን ለማስፈን በዲረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ሊኖረው እንደሚችል መረዳት አያዳግትም፡፡ አመራሩ ተጠያቂነት ለማስፈን የሚወስዳቸው እርምጃ በመረጃና ማስረጃ ላይ ሊመሰረት ስለማይችል ውጤታማ መሆን አያስችለውም፡፡ በመሆኑ ተጠያቂነት ከማስፈን አኳያ ተቋማቱ ስለሚሰጡት አገልግሎት በውጪ አካል ማስጠናት ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡*
- *በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የስነ ምግባር ደንብ/መመሪያ መኖሩ ማረጋገጥ ቢቻልም ሰነዶቹ የተዘጋጁበት ሁኔታ መኖሩ ይታያል፡፡ የተዘጋጁትም ሰነዶች የቆዩ በመሆናቸው ወቅታዊ በሆነ መንገድ በማሻሻል ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ ስራ እየተሰራ አለመሆኑን ተጠያቂነት ለማስፈን የሚደረገው እንቅስቃሴ ውስንነት ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ በስነምግባር ደንቦች ዙርያ የተዘጋጀ ስለጠና አለመሰጠቱ በሰራተኛው ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን ተጠያቂነት በማሰፈን በኩል የሚኖራቸው ሚና ውስን ያደርገዋል፡፡ ይህም የተቋም ሰራተኞች ተጠያቂነት ለማስፈን የሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ እክል ሊፈጥር እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ በተማሪም መረጃን በአግባቡ አደራጅቶ የመያዝ ልምድ አለመጠናከሩ በጥናት ሂደቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ በማስረጃ ላይ ተመስርቶ ተጠያቂነት ለማስፈን አዳጋች ሊያደርገው እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡*

- ሌላው ከተጠያቂነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የተቋም ስራ አፈፃፀም የገምገም ልምድ መኖሩ ቢታየም ድክመቶችን ለይቶ እርምጃ የመውሰድ ልምድ መኖሩ አመላካች መረጃዎች አልተገኙም፡፡ በዚህ ግምገማው ግኝት ላይ ተመስርተው እርምጃ የመውሰድ ልምድ አለመኖሩም አመራሩ ተጠያቂነት ለማስፈን የሚያደርገው ጥረት ክፍተት እንዳለ ማሳያ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በተቋማት ውስጥ ያሉ የስነምግባር ክፍሎች በአደረጃጀትና በሰው ሃይል ደካማ መሆናቸው የተጣለባቸውን ተጠያቂነት የማስፍን ሃላፊነት ለመወጣት እንዳይችሉ ማድረጉ የሚጠበቅ ነው፡፡ ክፍሉ በማጠከር ሚናው እንዲጫወት የማድረግ ስራ መስራት ከአመራረ ይጠበቃል፡፡ በተለይ ክፈሉ ሙስናንና ብልሹ አሰራር የመዋጋት አቅሙ እንዲያድግ አስፈላጊው ክትትልና ግምገማ ማካሄድ አመራሩ በተቋም ተጠያቂነት ለማስፈን የተጣለበትን ሃለፊነት አካል አድርጎ መውሰድም ይኖርበታል፡፡

4.3. የተቋማት ግልፅነት

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት በተዘጋጁ እቅዶች ላይ ውይይት በማድረግ እና በየደረጃው ለሚገኙና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማሳወቅ ወደ ስራ እየተገባ መሆኑን ለመልከት ተችሏል፡፡ በአፈፃፀም ሂደት ወቅትም የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ በተያዘላቸው ጊዜያት እንደሚካሄድ እንዲሁም የሚተላለፉ ውሳኔዎች የተለያዩ ዘዴዎችን (በፅሁፍ ሰነድ፣ በሶፍት ኮፒ እና በድህረ ገፅ) ለባለድርሻ እና ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንደሚደረጉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን የተለያዩ የመገናኛ አማራጮችንና ዘዴዎችን በመጠቀም (በጋዜጣ፣ በመፅሔት ወይም audio/video) ለሚመለከታቸው አካላት ይፋ እንደሚያደርጉ መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ተቋማቱ ከፍተኛ የግዥ ጨረታዎችን ግልፅ የማድረግ ስርዓት መኖሩ የግልጽነት አሰራር ባህል ስለመኖሩ ጠቋሚ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የየተቋማቱ ዋና ዋና እና አስፈላጊ መረጃዎች በተዘረጉ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በህትመት ውጤቶችና ድህረ ገፅ በህዝብ ግንኙነቶችና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራ ክፍሎች አማካኝነት በተደራጀ መልኩ ተደራሽ የማድረግ ስርዓት የተዘረጋ እና የሚጠቀሙ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት የተቋማት ግልፅነት ባህልና አሰራርን በማጎልበት በኩል የላቀ ፋይዳ እና የተጠያቂነት ለውጥ እያስገኙ ካሉ ስርዓቶች መካከል አንዱ የምርመራ ጋዜጠኝነት ባህል መኖር እና በአሰራራቸውም የየተቋማት ብልሹ አሰራሮች ለህዝብና ለመንግስት ማሳወቅ ወይም ማጋለጥ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት በሚያከናውኗቸው በርካታ የግዥ የተለያዩ ጨረታዎችና መሰል ጉዳዮች ላይ /ዙሪያ የምርመራ ጋዜጠኝነት ስራዎች የተሰሩ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ይህ የሆነበት የተለያ ምክንያቶች ቢኖሩም ከሙስናና ብልሹ ተግባራትን ጥቆማ የመስጠት ባህል አለመዳበር፣ ለውጥ አይመጣም የሚል አስተሳሰብ መኖር፣ የምርመራ ጋዜጠኝነት ባህል አለመዳበር ወዘተ… ሊሆን ይችላል እንጂ የዘርፉ ተቋማት የግዥና ጨረታ ሂደቶች ፍፁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዱ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ መሆን የለበትም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማት መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ መልካም የሚባል ልምድ እየጎለበተ መሆኑን ይታያል፡፡ ሆኖም ተቋማቱ ግልፅነት ለማበረታታት እንዲቻልና ሙስና እና ብልሹ አሰራር በመከላከልና ካለው ፋይዳ አንፃር ለምርመር ጋዜጠኞች ክፍት መሆናቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በዚህ ረገድ የምርመራ ጋዜጠኝነት ባህልና እንዲዳብር እንደ የህግ አውጪ መንግስታዊ አካልነታቸው ተቋማቱ የሚጠበቅባቸወን ሚና መጫወት ይኖሩባቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን መረጃ የሚጫወተውን ሚና ለሚገነዘብ ግልፅነት ሙስናን ለመዋጋት ምን ያክል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ህግ አውጪው አካል መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሙስናን ለመዋጋት ያለው ቁርኝነት የሚመዘነው ግልፅነትን በማበራታት የህብረተሰቡን ተሳተፎ ማሳደግ ሲቻል መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የተካተቱት ተቋማት በህግ በማውጣት፣ ህግ በማስፈጸም እና የዜጎችን መብትና ጥቅም በመስከበር ኃላፊነት የተጣለባቸው አካላት በመሆናቸው፣ በነዚህ አካላት የሚወጡና የሚዘጋጁ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ወቅታዊ በማድረግና የማሻሻል ስራ እንደሚሰሩና እነዚህንም ህጎች ለሚመለከታቸው አካትም ተደራሽ እንደሚያደርጉ መገንዘብ ተችሏል (የህትመትና የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም)፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚዘጋጁና በሚሻሻሉ የህግ ማዕቀፎች ለየተቋማቱ አመራና ሰራተኞች እና ለባለድርሻ አካላት በስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እንደሚዘጋጅ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ቀልጣፋና ምቹ ከሚያደርጉ ዘዴዎች መካከል አንዱ የዜጎች ቻርተር ማዘጋጀት እና የተዘጋጀውንም ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን በዚህ ረገድ የዘርፉ ተቋማት የቆዩ ቢሆንም የዜጎች ቻርተር በህመት ውጤቶች ደረጃ እና በተቋማት ግድግዳዎች ላይ ተቀምጠው ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህ ስርዓት ጋር በተያያዘ ነባራዊ የየተቋማቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት ተጨማሪ ዳሰሳ የሚፈልግ ሆኖ ይስተዋላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ ተቋማት አስፈላጊና ናቸወ የሚባሉ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች በማዘጋጀትና ማሻሻል በኩል ያለው እንቅስቃሴ እንደጥሩ ልምድ መውሰዱ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ህግ የማውጣት ሃላፊነቱም በአግባቡ አየተወጣ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ አዲስ የወጡ ወይም የተሻሻሉ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች ያመጡት ተፅእኖ በማጠናት በኩል ውስንነት ይታያል፡፡ በተለይ እነዚህ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች ሙስናንና ብልሹ አሰራር በመዋጋት በኩል ያስመዘገቡት ውጤት የሚያሳይ ጥናት መካሄዱ አመላካች መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ተቋማት በአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንደተሰራ ቢገለፅም የተፈጠረው ግንዛቤ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ስላበረከተው አስተዋፅኦ በቂ

መረጃ ማግኘት አልተቻልም፡፡ ግንዛቤ መፍጠሩ ውጤታማ የመከላከል ስራ መከወን አጋዥ ሚናው ካልተወጣ ከሃብት ብክነት የዘለለ ጥቅም አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ስለሆኑም የወጡት አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦች ውጤታመነት የመከታተል ተግባር ከአመራሩ ይጠበቃል፡፡

- የአገልግሎት አሰጣጥን በማጎልበት እና የተቋማትን ግልፅነትን በማስፈን ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የሚገመተው የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ እየተተገበረ መሆኑን ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ትግበራው ተቋማቱን ዜጎች በቀላሉ ገብተው ለመግለገል ያለቸው ልምድ የሚያግዝ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ተገልጋዮች ፍራቻ ሳይሰማቸው አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ለመፍጠር በሚያግዝ መልኩ ተደርጎ ሰነዱ መዘጋጀቱ የማረጋገጥ ሃላፊነት ተቋማት መወጣት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቋሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚታየውን የዜጎችና ባለድርሻ አካላት ተሳተፎ ውስንነት አንፃር የዜጎች ቻርተር መጠናት አለበት፡፡ የዜጎች ሰነድ መኖሩ ብቻ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ዋስትና የሚኖረው የዜጎች ግንዛቤ አድጎ ተግባረዊ ሲሆኑ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም የዜጎች ሰነድ በየጊዜው ወቅቱ በሚጠብቀው ደረጃ ማሻሻል አገልገሎቱን ከማሻሻሉ በተጓዳኝ የዜጎች ተሳትፎ ጊዜው የሚመጥን እንዲሆን አጋዥ ሚና ሊወጣ ይችላል፡፡

4.5. የተቋማት ንብረት አስተዳደር

በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ማንኛውም አይነት የንብረት አስተዳደር፣ የቋሚ ንብረት ምዝገባና ቁጥጥር ስርዓት የተጠናከረ እንደሆነ ቢገለፅም የዘርፉ ተቋማት ንብረቶች ማስቀመጫ ግምጃ ቤቶች እጥረት መስተዋሉ፣ ተቋማት ህንፃ የማደስ፣ህንፃ በመቀየራቸው ምክንያቶች የተነሳ የካይዘንን ስርዓት እና ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዳይዘረጋ በማድረግ አሰራሩ ለንብረት ብክነትና ብልሹ አሰራር ሊዳርግ መቻሉን መመልከት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ያሉ ተቋማት አመታዊ የንበረት ቆጠራ ማካሄዳቸው ቢታይም ብንብረት አስተዳደር በኩል ያሉት ችግሮች በመለየት የእርምት እርምጃ መውሰዳቸው የሚያሳ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ

በአብዛኛዎቹ የዘርፉ ተቋማት ወቅታዊ የንብረት አስተዳደር ስርዓት ‹IFMIS› ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተቋማት መመሪያውን ተከትሎ ንብረት የማስወገድ ስራ እንደሚሰራ በአካል በተደረገ ምልከታና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተቋማት ንብረት ዓመታዊመ ቆጠራ እንደሚካሄድ፣ መመሪያውን ተከትሎ ንብረት የማስወገድ ስራ እንደሚሰራ በአካል በተደረገ ምልከታና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በ2014 እና 2013 ላይ እንደ ዘረፍ በሰባት ተቋማት ላይ በአይነትም በገንዘብም ተለይቶ ተወግዷል፤ ከዚህ አንፃር በግልፅ ጨረታ በአይነት 113 ንብረቶች ሲሆኑ በገንዘብ 4,149,149.84 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ከ ሰማንያ አራት ሳንቲም) የሚገመት ንብረት ተወግዷል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በስጦታ የተሰጡ ንብረቶችን ስንመለከት በብዛት 167 የተለያዩ ንብረቶች በገንዘብ 4,967,027.5(አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሰባት ሺ ሃያ ሰባት ብር ከ ሃሳ ሳንቲም) ማወገድ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በንብረት አስተዳደርና ቋሚ ንብረት ምዝገባ እየተደረገ መሆኑ በበጎ ጎን የሚታይ ነው፡፡ ሆኖም ዓመታዊ ቆጠራ ስለ መካሄዱ መረጃዎች ቢኖሩም በቆጠራ ሪፖርት መሰረት ስለተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች የሚያሳይ ሰነድ አልተገኘም፡፡ ይህም በተቋማት ያለው የንብረት አስተዳደር ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ የዘርፉ ተቋማት ንብረት የሚያስተዳድሩበት መንገድ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በተጠናከረ መልኩ ለመዋጋት እንዲቻል ተደርጎ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘርፉ ተቋማት ንብረት ቆጠራና ንብረት ስርአት ተጠያቂነት በሚያጎለብት መልኩ መተግበር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በቂ የንብረት ማሳቀመጫ ቦታዎች አለመኖር በተካሄደው ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የመንግስትና ህዝብ ሃብት ለብክነት ሊጋለጥ እንደሚችል ያሳያል፡፡ የንብረት አስተዳደር

አሰራሩ በተገቢው ጥበቃና ቁጥጥር ካልታገዘ የመንግስት ንብረቶችን ለስርቆትና ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ያደርገዋል፡፡

- በተጨማሪም በየተቋማቱ የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ በአውቶሜሽን እና በካይዘን አሰራር የታገዘ ስለመሆኑ ማሳያ መረጃ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራር የተከተለ እንዳይሆን አድርጎታል ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡ ይህም ስርቆትና ብክነት ለመከላከል የሚያስችለውን እድል ያመክነዋል፡፡ የካይዘን ስርኣት አለመዘርጋቱ የሃብት አስተዳደሩ ዘመናዊነት ያለተከተለ ስለሚሆን ለብክነት የተጋለጠ ሊያድረገው እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ የተጠናከረ በአውቶሜሽን የታገዘ የንብረት አያያዝ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን ተደጋጋሚና አላስፈላጊ ግዥዎች ለመፈፀም በር ሊከፈት ስለመቻል ትኩረት ሊደረግበት ይገባል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የግዥ እቅድ እንደሚዘጋጅና በግዥ እቅዱ ላይ በሚመለከታቸው አካላት ግምገማዊ ውይይት እንደሚካሄድ እንዲሁም መጨረሻም በአፈፃፀሙ ሂደት ላይ ውይይት እንደሚካሄድ ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ግዥዎች ሲፈጸሙ ለሁሉም አቅራቢዎች የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ተደራሽ የሚደረግ መሆኑን በጥናት ወቅት ከታዩ መረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል ከግዥ ስርዓትጋር በተያያዘ የተነሳው ሀሳብ አሰራርና ስርዓት አኳያ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ከተስተዋሉ ክፍተቶች አንዱ በክምችት ክፍል ንብረቶች እያሉ ተመሳሳይ ንብረቶችን መግዛት፣ በአብዛኛዎቹ የገበያ ዋጋ ጥናት አለማካሄድ፣እቃዎች ንብረት ክፍል መኖርና አለመኖራቸውን የሚያረጋገጥ ስርዓት አለመዘርጋት እና የመሳሰሉት የአሰራር ክፍተቶች መኖራቸውን ከተደረገው ምልከታና የሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የግዥ እቅድ እንደሚዘጋጅና በግዥ እቅዱ ላይ በሚመለከታቸው አካላት ግምገማዊ ውይይት እንደሚካሄድ እንዲሁም መጨረሻም በአፈፃፀሙ ሂደት ላይ ውይይት እንደሚካሄድ ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በተደረገው ምልከታ እና በቀረቡ መረጃዎች መሰረት ከዘርፉ ካሉት በአራቱ ተቋማት በ2014 በፈጸሙት ግዥ በዕቅድ የ 23,123,356.86 600 አይነት ግዥዎች፣ ያለዕቅድ 11,414,267.63 ብር ዋጋ ያላቸው 446 ዓይነት ግዥ፣ በፕሮፎርማ ብር 18,080,071.96 ብር የሚያወጡ 415 አይነት ግዥዎች፣ በውስን ጨረታ ብር 4,961,832.78 ብር የሚያወጡ 52 አይነት ግዥዎች፣ ከአንድ አቅራቢ 6,359,235.26 ብር የሚወጡ 70 ዓይነት ንብረቶች ፣ በግልፅ ጨረታ 2,009,475.13 (180 ዓይነት ንብረቶች)፣ በዋጋ ማቅረቢያ 846,417.41 ብር ወጪ መደረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌሎቹ በዘርፉ ካሉ አራት ተቃማት ግን አንዳዶቹ ጥቅል ግዥ የሚያጀካሂዱ እንጂ በእቅድ የሚፈፅሙባቸው የግዥ አሰራር ወይም ስርዓት ስለመኖሩ አመላካች መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡

እንዲሁም ግዥዎች ሲፈጸም ለሁሉም አቅራቢዎች የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ተደራሽ የሚደረግ መሆኑን በጥናት ወቅት ከታዩ መረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል ከግዥ ስርዓት ጋር በተያያዘ የተነሳው ሀሳብ አሰራርና ስርዓት አኳያ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ከተስተዋሉ ክፍተቶች አንዱ በክምችት ክፍል ንብረቶች እያሉ ተመሳሳይ ንብረቶችን መግዛት፣ በአብዛኛዎቹ የገበያ ዋጋ ጥናት አለማካሄድ፣እቃዎች ንብረት ክፍል መኖርና አለመኖራቸውን የሚያረጋገጥ ስርዓት አለመዘርጋት እና የመሳሰሉት የአሰራር ክፍተቶች መኖራቸውን ከተደረገው ምልከታና የሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሌላው በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት በተረጋገጡ መረጃዎች መረዳ የተቻለው በአመዛኙ ዘመናዊ የግዥ ስርዓት (e-GP) ተግባዊ እያደረጉ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ከላይ ከተተነተኑት ከተቋማዊና መሰል ጉዳዮች በመነሳት በዘርፉ የሚገኙ ተቋት ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዱ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ የመንግስት ተግባራት አንዱ ግዥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ያለ እቅድ እና ቁጥቁጥ ላይ የተመሰረቱ ግዥዎች የሚዘወተር መሆኑን ነው፡፡ ያለእቅድ የሚፈፀሙ ግዥዎች በሥራ ክፍሎች ፍላጎት ላይ የመመስረት እደሉ አነስተኛ ከመሆኑ ባሻገር ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ የሚካሄድ አለመሆኑ አላስፈላጊ እቃዎች እንዲገዙ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ያለ ዕቅድ የሚገዙ ግዥዎች ቁጥራቸው ከፍተኛ መሆኑ ሲታይ ሂደቱ ለሀብት ብክነት የሚኖረው አስተዋፅኦ ክፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም አብዛኛው በተቋማት የሚፈፀሙ ግዥዎች በገበያ ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸው በምልክታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይ ግዢዎች በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ካልሆኑ በተጋነነ ዋጋ ላይ ተመስርተው እንዲፈፀሙ ሊደረጉ መቻላቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ ግዥ የሚፈፀምበት ሁኔታ መኖሩ ከፍተኛ የመንግስት መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት የስራ ዘርፍ ህጋዊ አሰራርና ስርዓትን ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡ እንዲሁም ለጥቅም ግጭት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- የግዢ ስርዓቱን ከሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል አስተዋፅኦ የሚኖረውን ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስርዓትን ሁሉም ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ተግባረዊ እየተደረገ አለመሆኑ ምልከታው ያሳያል፡፡ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉም ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ኤሌክትሮኒክ ግዥ ግልፅነት ለማስፈን ካለው ጥቅም ባሻገር ተጠያቂነት በሚያስከትል መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል ተገቢ ትኩረት ያሻዋል፡፡

4.7. ሰው ሃብት አስተዳደር

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአንድ ተቋም ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል ፋይዳ ካላቸው እና ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች ወይም የስራ ሂደቶች አንዱ የሰው ሃብት እንደሆነ ከተሞክሮና ከሚቀርቡ የሙስናና ብልሹ አሰራር ጥቆማዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ በሰው ሃብት ስር የሚከናወኑ መሰረታዊ ተግባራትን ለማሳለለጥ እንዲሁም ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተለያ ኮሚቴ አደረጃጀቶች ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዋና ዋና የሆኑ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን፣ ወዘተ ኮሚቴዎች መኖራቸው ሲሆን በዚህ ረገድ በዘርፉ ተቋማት እነዚህ ኮሚቴዎች መዋቀራቸውንና መደራጀታቸውን ከተሰበሰቡ በተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰው ሀብት ክፍል ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ የሰው ሀብት ቅጥር ሂደትን በግልፅ የማስተዋወቂያ መንገዶች ማለትም በጋዜጣ ፣ ድህረ-ገጽ፣ የውስጥ ሰሌዳ ወዘተ ተደራሽ እንደሚያደርጉ መመልከት ተችሏል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታ በአብዛኛዎቹ ተቋማት ብዙ ባይሆንም በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችን መፍትሄ ለመሰጠት ጥረት የተደረገ መሆኑን በምልከታና በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለአብነት ያህል በምደባ ፣በቅጥር ፣በዝውውር ፣የደረጃ ዕድገት እና ስልጠናና ትምህር በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ ቅሬታዎች እንደነበሩ ከመረጃዎች ማረጋገጥ ቢቻልም በወቅቱ ተገቢውን መፍትሄ እንደተሰጠ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ማብራሪያ ተሰጥቷል፤ነገር ግን ከዚህ ባለፈ ጉዳዮቹ/እነዚህ ቅሬታዎች ከፍ ወዳለ የፍትህ ስርዓት ያልቀረቡ መሆኑንም መገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የተቋማት የአመራር የስራ መደቦች ወይም ምደባዎች ከስራ ክፍል ስራ መሪዎች/ዳይሬክቶሬት ጨምሮ ወደ ታች የሚገኙ መደቦች በተዘጋጀ መመሪያ መሰረት በውድድር እንደሚፈፀም፣ ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃዎችም የማረጋገጥ ስራ እንደሚሰራ እንዲሁም የሰው ሀብት አስተዳደር ስርዓቱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀት ስራ እየተሰራ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

የዘርፉ ተቋማት የሰራተኞችና አመራሮች ሙያዊ ብቃትን የሚያሳድጉ እንዲሁም ሙያዊ ስነ ምግባርና የሚያጎለብቱ የማሻሻያ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እና ስልጠናዎች በሚጠበቀው ደረጃ እየተከናወኑ አለመሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ የተካሄዱትም የአቅም ግንባታ ቢሆን በሚጠበቀው ልክ ተደራጅተው የማይገኙ መሆኑን ከላይ ከቀረቡት ትምተናዎች በመነሳት የተወሰኑት ጉዳዮች በመልካም ሁኔታዎች ላይ የሚገኙ ቢመስልም ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ውጤታማ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ስለመሆናቸው ተጨማሪ ሌላ ዳሰሳ ይፈልጋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- ስልጠናዎች የማስፈፀም አቅም ከመገንባት በተጨማሪም የአስፈፃሚው አካል ስነምግባር በተተሸለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ አሰተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል እሙን ነው፡፡ ዕውቀትና ክህሎት በበጎ አመለካከት ካለተደገፉ ላልተፈለገ አላማ ሊውሉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ አንዱ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ከሚያግዙ ጉዳዩች ውስጥ የስነምግባር ማሻሻያ ስልጠና ነው፡፡ ሆኖም በዘርፉ ባሉት ተቋማት ለስነምገባር የሚሰጠው ስለጠና ትኩረት ተሰጥቶት በተደራጀና ውጤታማ በሆነ መልኩ አየተሰጠ አለመሆኑን ነው፡፡ ስልጠና መስጠቱ ብቻ ግን በቂ ላይ የሆን ይችላል፡፡ ስልጠናው በፍላጎት ዳሰሳ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ ስልጠናዎች በፈላጎት ዳሰሳ ላይ መመሰረታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተቋመዊ በፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ ስልጠና የሰራተኛውን አቅም ልማት ሊያግዝ ቢችልም የማስፈፀም አቅም ክፍተቶች በመሙላት በኩል ሊኖረው የሚችለው ሚና ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ተቋማት ግልፅ የሆነ የስልጠና ፖሊሲ በመንደፍ አላማቸውን ከዳር ለማደረስ የሚስችላቸውን የስልጠና መረሃግብርና አሰራር መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ስርዓትን ተግራዊ ማድረግ እንደሚገባቸው ህግ በህግ ተደንግጓል፡፡ ይህም ስርዓት መተግበር ከጀመረ ከአስር ዓመት በላይ እንደሆነው ይታወቃል፡፡ በነዚህ ጊዚያት ውስጥ ሁለት ዓይነት የምዝገባ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ካለፉት ሶስት ዓመታት ጀምሮ ሃብታቸውን ማሳወቅና ማስገንዘብ የሚገባቸው አካላት በኤሌክትሮኒክስ ‹ኦን ላይን› ምዝገባ ስርዓት ሃብታቸውን እንዲያስመዘግቡ በቂ የሚባል ግንዛቤ ስራዎች መሰራታቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከተሰበሰቡ መረጃች መገንዘብ የተቻለው አብዛኛዎቹ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት በቀድሞ የምዘገባ ስርዓት ማለትም በተዘጋጀው ሰነድ ቅፅ ምዝገባ ያደረጉ መሆኑ ቢተወቅም ካለፉት ሶስትና ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን በተዘረጋው የ‹‹ኦን ላይን› ምዝገባ መንገድ አጥጋቢ አመሆኑን በተደረጉ ውይይቶች መገንዘብ ቢቻልም፣ በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ የምዝገባ ሂደቶች በዘርፉ ካሉት ተቋማት 2896 ከሚጠጉ ሰራተኞች ውስጥ 2612 ሰራተኞች እና 98 አመራሮች ሃብታቸውን እንዳስመዘገቡ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ሆኖመ ግን በባለፉት ዓመታት የተዘረጋውን የኦን ለይን ምዝገባ ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ለተስተዋለው መዳከም እንደ ምክንያትነት ከቀረቡ ጉዳዮች መካከል የ‹ኦን ላይ› ስርዓት ዙሪያ ክፍተት መስተዋሉ/ አለመስራቱ፣ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች መቀያየር፣ ስርዓቱን በማሳሰብና በማሳወቅ በኩል ደካማ ክትትል፣ ስርዓቱ ምንም ዓይነት ለውጥ አያመጣም የሚል የማጥላላት አስተሳሰብ ወዘተ… ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለዚህ የተዘረጋው ስርዓት በአግባቡ ተግባራዊ አለመሆኑ ስረዓቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል ሊያበረክት የሚገባውን አስተዋፅኦ ደካማ ማድረጉን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- የንብረት ማሰመዝገብ ስራው በአጥጋቢ ሁኔታ የተካሔደ መሆኑን ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ አብዛኛው በኦን ላየን የተመዘገቡ አለመሆናቸው ሲታይ ደግሞ

አፈፃፀሙ ላይ ውስንነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ዋና ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው የኦን ላየን ሲስተሙ ከኢንተርኔት መቆራረጥ ተያይዞ በሚፈጠሩ ችግሮችም በምዝገባው ሂደት እክል መፍጠሩ ተጠቅሷል፡፡ እንደ ህግ አውጪ አካል ደግሞ የምዝገባ ሰነዶች አጣርቶ ለሌሎች አብነት የሚሆኑ እርምጃወች ቢወሰድ ኖሮ አፈፃፀሙ አስተማሪነቱ የጎላ ይሆን ነበር፡፡ መመዝገቡ ተጠያቂነት ማስፈን ካልቻለ ግቡን መቷል ብሎ መውሰድ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ስነምግባር ክፍሎች የንበረት ማስመዝገብ ስራው ዘመናዊነት እንዲላበስ በማደረግ በኩል ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

4.9. ኦዲትና ቁጥጥር

የኦዲት አሰራር ስርዓት ቁጥጥር በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል፣ በመቆጣጠር እንዲሆን የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ በማድረግ እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ የተጠያቂነት ስርዓትን በማጎልበት የሚኖራቸው ሚና የላቀ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የኦዲት ስራዎች ተደራጅተው የሚገኙ መሆኑ ቢገለፅም ለአብነት ያህል በሁሉም ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች የተገኙ ቢሆንም) የውጪ ኦዲት ሪፖርቶችን በሚመለከት ግን የመውጫና የመግቢያ ቃለ ጉባኤዎች ካልሆኑ በስተቀር የኦዲት ሰነድ ሪፖርቶችን /ሰነዶች ለማግኘት አልተቻለም፡፡ የውስጥ የኦዲት ሪፖርቶች እና የተሰነዘሩ የማሻሻያ ሀሳቦችም በአንዳንድ ተቋማት ተደራሽነታቸው ላይ ውስንነት ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ በዘርፉ ተቋማት ስለልተወራረዱ፣ አልግባብ የተወሰኑ እና ያላግባብ ተወስደው ተመላሽ ስለተደረጉ ግኝቶች ወይ የገንዘብ መጠን በግልፅ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው፤

- ከተሰበሰበው መረጃ መረጃ የሚቻለው ነገር ቢኖር በዘርፉ ባሉ ተቋማት የውስጥና ውጭ ኦዲት መረጃ አያያዝ ላይ ክፍተት እንዳለ ነው፡፡ አንዱ ማሳያም የውጭም ሆነ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት መረጃ በመሰብሰብ ሂደቱ ላይ ማግኘት አለማቻሉ ነው፡፡ ይህ በዘርፉ ባሉ ተቋማት በኦዲት ሪፖረቶች ላይ ተመስርተው የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎችና

ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው ማግኘት አልተቻለም፡፡ የተሰሩ ስራዎች የሉም ብሎ መደምደም የተሳሳተ ሊሆን ቢችልም የተሰሩ ስራዎች ተሰንደው ባለመቅረባቸው በመረጃና ማስረጃ ላይ የተሰመረቱ መሆናቸውን ግን እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በዘርፉ በኦዲት ዙሪያ የሚታየው ልምድ በየጊዜው የሚታዩ ክፍተቶች በማረምና ጥንካሬዎች በማስቀጠል የመንግስት ሀብትና ንብረት ማስተዳደር ላይ ውስንነት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡

- ሌላው በዘርፉ ተቋመት የታየው ክፍተት የውስጥና ውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው አካለት ተደራሽ መሆናቸው የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ ነው፡፡ ሪፖርቶቹ ተደራሽ አለመሆናቸው ግልፅነትና ተጠያቂነት ለማስፍን የሚደረገው እንቅስቃሴ ክፍተት የሚስተዋልበት መሆኑን ነው፡፡ ክፈተቱም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተከሰቱት ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ አስተያየት በማቅረብ አሳታፊ በሆነ መልኩ ሙስናንና ብለሹ አሰራር ለመዋጋት ያለው እድል ያጠበዋል፡፡ በተጨማሪም የውስጥና ውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ተደራሽ አለመሆናቸው ለምሳሌ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሆነም የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጃቶች ሙስናን የሚስችላቸውን መድረክ ውስን እንዲሆን በማደረግ ውጤታማ ተሳትፎ እንዳያደርጉ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል የሚጠበቅ ነው፡፡

4.10. የሙስና ስጋት ልየታ

ተቋማት የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት ለለመወጣት የዘረጉትን ስርዓትን፣ አደረጃትን፣ የስራ ክፍሎች ወይም የስራ ሂደቶቻቸውን መሰረት በማድረግ አጠቃላይ ለሙስና ብልሹ አሰራሮች ያላቸውን የተጋላጭነት ደረጃ እና ገፅታ በየወቅቱ መዳሰስ እንደሚገባቸው ይታወቃል፡፡ ይህ የዳሰሳ ምልከት አሰራር ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል የተቋማትን ተልዕኮ ውጤታማ በማድረግ፣ ተቋማት መልካም አገልግሎት አሰጣጥ በማሳደግ፣ ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር ወዘተ… በተገልጋዩ ህብረተሰቡ ዘንድ የተቋማትን ተዓማኒነት በማግኘት ያለው ፋይዳ የላቀ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አይነት አሰራር የላቀ ሙያዊ ትጋትና ስነምግባር የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋማት ትኩረት ሰጥተው በስነምግባር መከታተያ ክፍል ወይም በሌላ አካል መስራት እንደሚገባቸው ግንዛቤያቸው ሊጎለብት ይገባል፡፡ መንግስት ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ሁኔታን በስራ ሂደት ወይም በአደረጃት ወዘተ… መሰረት በማድረግ ዳሰሳዊ

ጥናቶችን ማካሄድ እንደሚገባቸው በተሻሻለው የስነምገባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 1236/2013 ተደንግጓል፡፡ በተቋምዎ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ስጋት የሆኑ የስራ ሂደቶችን ይዘርዝሩ፣ የመከሰት እድልን እና ተጸዕኖን (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ) ልየታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1.	ግዥና ፋይናንስ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	✓ መመሪያን አለመከተል ✓ ውሎች መብትና ግዴታዎችን ያላሟሉ ሆነው መቀረፃቸው ✓ የፕሮፎርማ አሰባሰብ፣ የጨረታ ሂደት	✓ በመመሪያው መሰረት መስራት/ ተጠያቂነትን ማስፈን ✓ ውሎች ሲዘጋጁ የህግና የስነ ምግባር ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡ ቢደረግ
2.	ሰው ሃብት	መካከለኛ	ከፍተኛ	✓ ሚስጥር አለመጠበቅ ✓ ካለአግባብ የጡረታ ዘመን ማራዘም ✓ ብቃት ያለው ሠራተኛ አለመቅጠር፣ ቅጥር፣ ዝውውር እና እድገት በህጉ መሰረት መስራት	✓ ሙያው የሚጠይቀውን ስነ ምግባር መላበስ ✓ በመመሪያው መሰረት መስራት/ ተጠያቂነትን ማስፈን ✓ በውድድር ብቃት ያለውን በቅጠር፣ በህጉ መሰረት ማዛወር፣ማሳደ ግ
	ጠቅላላ	ከፍተኛ	ከፍተኛ	✓ የቁጥጥራና	✓ ተገቢ የሆነ

	አገልግሎት			ተጠያቂነት ማነስ ✓ መመሪያን አለመከተል	ቁጥጥር ቢደረግ ✓ መመሪያ ተከትሎ ቢሰራ
3.	ትራንስፖርት ስምሪት	መካከለኛ	መካከለኛ	✓ የመኪና አገልግሎት፣የነዳጅ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው አካላት በህግ ያለመወሰን	✓ ለነዳጅ እና ለተሽከርካሪ አጠቃቀም ህጋዊ መመሪያ ማውጣትና መተግበር
4.	ንብረት	መካከለኛ	ከፍተኛ	✓ ጥራት የሌላቸው ንብረቶች መረከብ ✓ የቁጥጥራና ጠያቂነት ማነስ	✓ በአግባቡ ንብረትን መያዝና መጠበቅ ✓ ተጠያቂነትን ማጠናከር፣ የዳበር ኦዲት ስርዓት

በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ከተመለከታቸው ጉዳዮች አንዱ የጥናት ዘርፎችን ተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ መመልከት ሲሆን በዚህ ሃሳብ መሰረት ከዘርፉ ተቋማትን የተሻለ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ረዘም ያለልምድና ሙያዊ እውቀትና የረዥም ጊዜ ልምድ ባላቸውና የተቋማቱ ሰራተኞችና የስራ ሀላፊዎች ከተሰበሰቡ መረጃዎች መገንዘብ ወይም ማጠናቀር የተቻለው በአብዛኛዎቹ የዘርፍ ተቋማት የግዥና ፋይናንስ፣የሰው ሀብት አስተዳደር፣ንብረት አስተዳደር፣ጠቅላላ አገልግሎት በከፍተኛ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ደረጃ እንደሆኑ የተቀመጡ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የትራንስፖርትና ስምሪት አገልግሎት ደግሞ በመካከለኛ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ደረጃ የሚገኙ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ ከተቋሙ ልዩ በህሪ አኳያ በኢትዮጵያ ብዙሀን መገናኛ ባለስልጣን ከስራ ዘርፎች መካከል የፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ከፍተኛ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ደረጃ ላይ መሆኑን ተጠቁሟል።

ክፍል አምስት

መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

5.1. መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ በማዕድን ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡- 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖረቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

- በዘርፉ ባሉት ተቋማት የስነምግባር ክፈሎች መዋቅር ደረጃ የሚታዩ ቢሆንም በቂ የሰው ሃይልና ሃብት የተመደበላቸው አለመሆኑን ታይቷል፡፡ አመራሩም ለክፍሉ የሚሰጠው ትኩረት ከክትትል እና ድጋፍ ማነስ አኳያ ሲታይ ውስንነት እነደሚታየው ነው፡፡ በተጨማሪም ተቋማቱ በአዋጅ የተደነገገውን መዋቅር በመተግበር በኩል ያለቸው ዝግጅነት አነስተኛ እንደሆነ ለመግነዘብ ይቻላል፡፡ ስነምግባር ክፍሉ በቀጥታ ተጠሪነቱ ለተቋም አመራር መሆኑን ለጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡
- በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርከታ ላይ ጥልቀት ያላቸው አለመካሄዳቸው እንደማሳያ ሊቅርቡ ይችላሉ፡፡ ሙስና እና ብልሹ አሰራር አሳታፊ እና ጥናት ላይ ተመስርቶ የመከላከል ስራ እየተሰራ አለመሆኑን መግነዘብ ይቻላል፡፡
- የመረጃ ተደራሽነት ሰራዎችም እስከ ሰራተኛው ድረስ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ግልፅነትን ማስፈን የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን መመልከት ቢቻልም የችግሩነ ክብደት በሚመጥን ደረጃ ላይ ነው ብሎ መውሰድ የተሳሳተ ድምዳሜ ሊያድርስ ይችላል፡፡
- በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል በተደራጀ መልኩም ባይሆን ስለጠና (ግንዛቤ) የመስጠት ልምድ እንዳለ መመልከት ተችሏል፡፡ሆኖም ህጎችን ለማሻሻልና አዳዲስ ለማውጣት የሚያስችሉ አሰፈላጊ ጥናቶች የማካሄድ ስራ ተግባራዊ

አለመሆኑን የስነምግባር ደንበሰ እና የዜጎች ሰነድ ለረጅም ጊዜ ሳይሻሻሉ መቆየታቸው አመላካች ነው፡፡

- በተቋማቱ ያለው የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን ስርኣት እና የአውተሜሽን ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
- አብዛኛው የተቋማት ግዝዎች በቁጥቁጥ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ግዥዎች ያለ እቅድ የመፈፀም ሁኔታዎችም ታይቷል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ውስጥ ሀሰተኛ የትምህርትና ስራ ልምድ ሰነዶች የማጣራት ስራ ተተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡ በተጨማሪም በፍላጎት ዳሰሳ ላይ የተመሰረተ የስነምግባር እና አቅም ግንባታ ስለጠና አየተሰጠ አመሆኑን መረጃዎች ያመላከታሉ፡፡
- ሃብት የማሳወቅና ማስመዝገብ ስራ አጥጋቢ ሊባል በሚል ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ምዝገባው ላይ ተመስርቶ ተጠያቂነት ማስፍን ላይ ግን ክፍተት መኖሩን ተገቢ ነው፡፡
- የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙሰናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡
- በዘርፉ ውስጥ ያሉ ተቋማት እንደ ህግ አውጪ አካል በተጠኑት ጉዳዮች ላይ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ከሌሎች ተቋማት የተለየ ተግባር ተፈፅሞ አለመታየቱ ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡

5.2. መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

ከላይ ከቀረበው ትንተና በዘርፉ የሚስተወቃሉ ወይም ለሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ገፅታን ለማሻሻል የሚከተሉት ተግባራዊ ሊሆኑ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋር የሚከተሉት ሃሳቦች ሊተገበሩ ይገባል

- የዘርፉ የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች በተቋማቸው የስነምግባር ክፍል አደረጃጃት በመፈተሽ አስፈላጊው የማጠናከር ስራ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዘርፉ ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች፣ አስፈላጊ ቁሳቁስ፣ በበጀት፣ ሥራ ቦቻ ምቹነት ወዘተ እንዲያጠናክሩ በማድረግ የሥራ ክፍሎቹ በህግ የተሰጣቸውናና የሚጠበቅባቸውን በተቋም ደረጃ ሙስናና ብልሹ ተግባራትን የመከላከል ኃላፊነታቸውን ተጠያቂነት በሚያስከትል ደረጃ ስራቸውን እንዲያከናው የማድረግ ስራዎችን ማጠናከር ተገቢ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም በተቋም ውስጥ ሙስናን የመከላከል ስራ በተቀናጀ መልኩ ለመከላከል የሚያስችል አደረጃጀት መዘርጋት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ የተለያዩ የስራ ክፍሎች በይበልጥ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመከላከል የላቀ ፋይዳ ያላቸው የስራ ክፍሎች ለምሳሌ የኦዲት፣ የህግ፣ የንብረት አስተዳደር፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር ክፍሎችን ከስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር በቅንጅት የሚሰሩበትን ስርዓት መዘርጋትና ማጠናከር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች በተለያዩ የሙያ እና የስነምግባር ደረጃ የሚያጎለብቱ የየተቋማትንና የሙስናና ብልሹ ተግባራት ለመከላከል የሚወጡ ህጎች እና ስርዓቶች ዙሪያ የግንዛቤና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር ያስፈልጋል፣
- የግልፅነት ባህልና ስርዓትን ለማጠናከር እንዲሁም የተገልጋዩን አመኔታ ለማጎልበት ተቋማት ስለሚሰሩር ስራ እና እንቅስቃሴ በሚዲያና የህትመት ውጤቶች ተደራሽ የሚደረግበትን አሰራርና ስርዓት ማጠናከር፣

- በሃብት ምዝገባው ሰነድ ላይ ተመስርቶ የመጣራት ስራ መስራትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ከተቋም አመራር ይጠበቃል፡፡ የጥቅም ግጭት ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በተጠና መልኩ ተግባራዊ ማደረግም አጋዥ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ ረገድ በቅርብ ዓመታት በተጀመረው የኦንላይን ምዝገባ ስርዓት ግልፅነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት መንገድ የመተግበር ስራ ከተቋማት ይጠበቃል፡፡
- የተዘረጉ የሙስናና ብልሹ ትግባራት መረጃ የሚገኙባቸውን የጥቆማ መስጫ ስርዓቶች ዲጂታል አሰራርን ጨምሮ በተለያዩ አማራጮች ማጠናከር፣ በተገኘው መረጃ ላይ ፈጣን ማጣራት በማደረግ እርምጃ የመውሰድ ልምድ ማዳበር ተገቢ ነው፡፡
- በዘርፉ ተቋማት የሚወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ከማደረግ በተጨማሪ በተደራጀ መልኩ ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ ተከታታይነት ያላው ስልጠናዎች ማካሄድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- ሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል ረገድ ያላቸውን ፋይዳ በመረዳት የኦዲት የስራ ክፍሎች የሚሰጡትን አስተያየት ተግባረዊ እና ተደራሽ የማድረግ እንዲሁም በዚሁ ሪፖርት መሰረት ተጠያቂ የሚሆኑ አካላትን ተገቢ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ አሰራር ማጠናከር፣
- የንብረት አስተዳደር ስርኣት የሚያዘምኑ ስርአቶችና አሰራሮች ተግባራዊ በማደረግ ብክነትን የመከላከል ስራ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ የአውቶሜሽን ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የሙስና ስጋት ተጋላጭ እና የተግልጋዮች እርካታ ላይ ጥልቀት ያለው ጥናት ማካሄድም አሰፈላጊ ነው፡፡
- የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችንና ለክፍሉ አጋዥ የሚሆኑ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት በታቀደና በተደራጀ መንገድ ጥናት እንዲያደርጉ በማድረግና በተጠኑት ላይ ከተቀመጡበት የሙስና ስጋት ደረጃ የተስተዋሉ ለውጦችን በየጊዜው መከታተል ይገባል፡፡

References

1. Cecilia Testa (2003, November) Government Corruption and Legislative Procedures: is One Chamber Better than Two? London School of Economics and Political Science Houghton Street(https://eprints.lse.ac.uk/6642/1/Government_Corruption_and_Legislative_Procedures_is_One_Chamber_Better_Than_Two.pdf accessed on April 23, 2023)
2. Harutyunyan, Khachik (2021, April) The Role of Parliaments in the Fight Against Corruption, Westminster Foundation for Democracy (https://www.wfd.org/sites/default/files/2022-05/2021-04-khachik-anti-corruption-paper.pdf accessed on April 23, 2023)
3. Davies, Joanne (2009) Parliamentarians And Corruption In Africa: The Challenge of Leadership and the Practice of Politics, The African Parliamentarians Network Against Corruption (APNAC) (http://old.agora-parl.org/sites/default/files/challenge_of_leadership.pdf accessed April 23, 2023)
4. OECD (2017), Preventing Policy Capture: Integrity in Public Decision Making, OECD Public Governance Reviews, OECD Publishing, Paris.